# ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞ ቅጽ 46 ቁ. 3 ሚያዚያ 2013 ዓ.ም.

## ልጓም የሌለው አምባገነን መቆሚያው ገደል!

ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛና መነሻ ብቻም ሳትሆን የተለየዩ ነገዶች መግቢያም መዳረሻም ነበረች። ከረዥም ዘመን ጀምሮ አገራችን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆኑ  የአፍሪካ፣ የአረቡና የእስያ ሕዝቦች ከደቡብና ከሰሜን የሚገናኙባት ፤ የሚስተናገዱባት ብለውም በሀገርነት ወደዋትና ፈቅደዋት የሚኖሩባት የኅብረ-ሕዝብ መናኸሪያ ሀገር ሆና ቆይታላች።

ኢትዮጵያ በየዘመኑ የተነሱ ታላላቅ ሃይማኖቶች መዳረሻ ሀገር በመሆን ከብዙዎች ጥንታዊያን ከሚባሉ ሀገራት ተርታ የጎላ ታሪክና ዝና አላት።ኢትዮጵያ እንደሀገር ብሎም እንደመንግሥት የቆየ የፖለቲካ ታሪክ እንዳላት ታሪክ የመሰከረው ነው። በዓለም ላይ ካሉ ሀገራት በመንግሥትነት ዛሬ ከኢትዮጵያ ጋር ሊስተካከል የሚችል ታሪክ ያላቸው ቢኖሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው ማለት ይቻላል።

አገራችን ኢትዮጵያ እንደ አባይ፣ ቀይባህርና የገልፍ ባህረሰላጤን የመሳሰሉ የዓለም አቀፍ እድገቶች አቋዳሽና ተቋዳሽ ሆና ቆይታለች። ከቀይባህር ወዲህና ወዲያ የነበረውን ዓለም አቀፋዊ የንግድ እንቅስቃሴ ህንድ ውቅያኖስን በዘመኑ ይቆጣጠር የነበረው የአክሱም ዘመነ-መንግሥት በዓለም ከነበሩት ጥቂት ኃይላት ውስጥ አንዱ ነው። የኢትዮጵያ የመንግሥት ታሪክ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን እንዲኮሩበት የሚያደረገው ሌላው ገጽታው  ሁሉም ሕዝቧ በውህደትም ሆነ በተናጠል የተሳተፉበትና የተጋሩት በመሆኑ ነው። በተለያዩ ወቅቶች የሀገራችን ከፍሎች በመንግሥት ደረጃ ተዋቅረው የነበሩት ተደጋግሞ የሚነሱት የአክሱምና የጎንደሩ ሥርወ መንግሥታት ብቻ ሳይሆኑ የሰለሞናዊ ፣ የዛጒዌ፣ የየጁ፣ የሀድያ፣ የሐረር፣ ...ወዘተ እየተባሉ የሚጠሩትም ሥርወ- መንግሥታት መኖር የሚያረጋግጥልን ይህንኑ የታሪክ እውነታ ነው። አሁን የምንኮራበት የአስተዳደርና የወታደራዊ ጥበብ፣ የሥነጥበብና የሥነጽሁፍ፣ የሥነህንፃ፣ የእርሻና ቴክኖሎጂ ...ወዘተ ሀገራዊ ቅርስ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን የወል አስተዋጽዖ ውጤት ነው።ኢትዮጵያውያን አሁን የምንኮራበት የአገር ፍቅር፣ ወኔ፣ ድፍረት፣ አስተዋይነት፣ በራስ መተማመን፣ ...ወዘተ ከዚህ የረዥም ዘመን በመንግሥትነት ደረጃም ጭምር ሥርዓት አበጅቶ ለመኖር የመቻል ባህልና ተመክሮ የሀገር ባለቤትነትና የአንድ ሕዝብነት አስተሳሰብና ንቃተ- ህሊና መስረፅ እርስ በርስ ከተጋመደ ትስስርና ከሌሎችም የማኅበራዊ በይነ-ግብርና የታሪክ ክንውኖች ክምችት የሚቀዳ ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በባህልና በቋንቋ፣ በሃይማኖቶችና እምነቶች የተለየየ ኅብረቀለም ያሏት ሀገር እንደመሆኗ መጠን በአንጻሩም በነዚህ ልዩነቶች ዙሪያና በሌሎች ነገሥታት የጦር አበጋዞችና አምባገነኖች በፈጠሯቸው የሥልጣን ሽኩቻዎች ስትናወጥ ኖራለች። ከነዚህ ልዩነቶች  የመነጩ የእርስ በርስ ጦርነቶች ዛሬ ሲታዩ ጉድፍ/ጠባሳ ብቻ ሳይሆን መልካም ነገርም ትተውልን አልፈዋል። የባህል፣ የእምነትና የሃይማኖት  መወራረስን፤ የሕዝብ አካላዊ መቀላቀልና እንዲሁም ተቻችሎ መኖር የሚያስችል የማዕከልና የአካባቢ አስተዳደር ግንኙነትና ጥበብ እንዲሁም ብርቅና ድንቅ የሆኑ በርካታ እሴቶቻችን እንደአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

በክርስትና ሃይማኖት ተከታዩ በአፄ ልብነድንግልና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዩ በአህመድ ግራኝ መካከል የተደረገው ታላቅ ጦርነት በሕዝብና በሀገሪቱ ላይ ያስከተለው እልቂትና ውድመት ከፍተኛ ቢሆንም፤ ከጦርነቱ በኋላ የሁለቱ እምነት ተከታዮች በአንድ መንደር እያደገም በአንድ አካባቢና ሀገር ተባብሮና ተቻችሎ መኖር የሚያስችል የኃይል ሚዛን ተፈጥሮላቸው እንደነበር ታሪክ የመዘገበው ሐቅ ነው። የየአካባቢው ነገሥታት በማዕከላዊ ነገሥታት ሥር የውስጥ ነፃነታቸው አንፃራዊ በሆነ ደረጃም ቢሆን ተከብሮና ተጠብቆ ባንድ ሀገር ውስጥ ሁለት አስተዳደሮች ተቻችለው የሚኖሩበት የፖለቲካ ባህል እንዲሁ የሚፈጠር ሳይሆን ፤ ከተራዘመ ግጭት የሚመነጭ ትምህርትና አብሮ የመኖር የጋራ ፍላጎትም ውጤት ጭምር መሆኑን ነው ታሪካችን የሚያሳየን።

ይህ ረዥም ዕድሜን ያስቆጥረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ መንግሥት ታሪክ፤ ዜጎች ረጅም ጊዜ ለኖሩበት አንድነታቸውና ውህደታቸው ማስረጃና መገለጫም ጭምር ነው። የአንድነታቸውንና የውህደታቸውን እውነታነት የተሟላና የጎላ የሚያደርገው ሌላው የታሪካቸው ገፅታ ደግሞ በፍልሰት አማካኝነት የፈጠሩት መስተጋብር ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰሜኑ ወደ ደቡብ፤ የደቡብ ወደሰሜን፤ የምስራቁ ወደ ምዕራብ፣ ወይም በተቃራኒው አቅጣጫ፣ …ወዘተ በመፍለስ በደም ተሳስረዋል፤ ተቀላቅለዋል፤ እምነት፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ጥበብ፣ …ወዘተ ጭምር ተወራርሰዋል። ይህ የውህደትና የመጋመድ ሂደት ደግሞ በሰላም ሳይሆን በአብዛኛው ብዙ እልቂት ባስከተለ ጦርናትና ረዥም ዘመን በአስቆጠረ የርስ በርስ ግጭት ጭምር ማለፉንና የረዥሙ የአገር ግንባታ ታሪካችን አካል መሆኑን ያነሳነው ለአሁኑም ሆነ ለመጪው ትውልድ ትምህርትና ተመክሮን የሚያስጨብጥ፤ ኢትዮጵያዊነቱን በሚገባ እንዲረዳ የሚያስችል ታሪካዊ ፋይዳ ይኖረዋል ከሚል እሳቤ በመነሳት ነው። አገራችን ያለፈችበት የአገረ መንግሥት ምሥረታ ሂደት በኢትዮጵያ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በዓለም ላይ ባሉ የተለያዩ ሀገራት የነበረና ያለ ዕውነታ ነው።

በዛሬው የዴሞክራሲያ እትም ከላይ ለዘረዘርነው አቢይ ጉዳይ ትኩረት የሰጠንበት ምክንያት አዲሱ ትውልድ የሀገሩንና የሕዝቡን ጥንታዊ ታሪክ እንዲሁም ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደቶች አልጋ ባልጋ እንዳልነበሩ በሚገባ እንዲገነዘብ ለማደረግና ትውልዱም በራሱ ዘመን ለሀገር ግንባታ ማበርከት የሚገባውን አስተዋጽኦ በሚገባ መወጣቱን እንዲጠይቅና ካለፈውም እንዲማር በማሰብ ጭምር ነው። ትውልድ የሚለካው፣ የሚፈረጀው እና የሚዘከረው በነበረት የታሪክ ዘመን ውስጥ ባበረከተው አዎንታዊና አሉታዊ አስተዋጽአው ነው። ስለኢትዮጵያዊነትና ስለኢትዮጵያዊ ታሪክ ስናነሳ የዚያን ለውጥ ናፋቂ ፤ ለአገሩ ቅን አሳቢ፤ ሕዝብ አፍቃሪ፤ ተመራማሪና አይበገሬ ጀግና ትውልድ ታሪክን ወደኋላ መለስ ብሎ መቃኘቱ ግንዛቤን የተሟላ ያደርጋል። የትውልዱን ኢትዮጵያውነት ቅኝት፤ ባጠቃላይ ለሰው ልጆች በተለይም ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የነበረውን ክብር፣ ለእኩልነት ለፍትኅና ለመብት መረጋገጥ ይሰጥ የነበረውን ሥፍራ በሚገባ መረዳቱ ለቀጣዩ ትግላችን ትልቅ ተመክሮንና ትምህርትን የሚያስጨብጥ ሆኖ እናገኘዋለን። አገራችንና ትውልዱ አሁን ያሉበትን አስቸጋሪና ውስብስብስ የታሪክ ክስተት በሚገባ መመርመር፣ ሀገሪቷ ከገባችበት የፖለቲካዊ፣ የማኅበራዊና የኤኮኖሚያው ቀውስና ትርምስ እንዴት ልትወጣ ትችላለች? ሕዝባችንም ከገባበት የመከራና የጨለማ ዘመን ተላቆ እንዴት ወደ ሰላምና መረጋጋት፣ እንዲሁም የእደገትና የልማት ጎዳና መጓዝ ወይም መሸጋገር ይችላል? ለሚሉት ቁልፍ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ያስችላል። ውስብስብ ለሆኑ እና ልዩ ልዩ መልክ ላላቸው የአገሪቱ ችግሮች አማራጭ የሆኑ የመፍትሄ ሀሳቦችንም ለመጠቆም ይረዳል።

ታሪካችንን መለስ ብለን ስንቃኝ ኢትዮጵያ የገናና ታሪክ ባላቤት ለመሆን የበቃችው በጀግኖቿ ብልህና የሰከነ አመራር ብቻ ሳይሆን ኃላፊነትን ለመሸከምና የትውልድ አደራን ለመወጣት ብቁ የሆነና መስዋዕትነትን የሚከፍል ወጣት ትውልድ ያለማቋረጥ በማፍራቷ ጭምር ነው። ለረጅም ጊዜ በቆየው በሀገራችን የኅብረተሰብ ታሪክ ውስጥ የተመዘገቡ የገድል ታሪክ ምዕራፎችም የሚመሰክሩት ነገር ቢኖር ይህንኑ ሐቅ ነው። ለዚህም መገለጫው በተጻፈውም ሆነ ባልተጻፈው የትውልድ ታሪካችን ውስጥ እንደ ምሳሌ (ሞዴል) የሚወሱት ጀግኖቻችን ሀገራዊ ግዳጅ የተረከቡትና ያከናወኑት በወጣትነት እድሜያቸው ነው። ከቅርብ ጊዜ ታሪካችን ብንጠቅስ እንኳን ከፋሽስት ጣሊያን ወረራ በኋላ የመጣው ኢትዮጵያዊ በተለይም ዘመናዊ ትምህርት ለመቅሰም እድል ያገኘውና የተማረው ትውልድ የኢትዮጵያን ሁኔታ እንዴት መለወጥ እንደሚችል አምርሮና አጠንክሮ መጠየቁን፣ መመራመሩንና መፍትሔ ለመሻት መሞከሩን እንረዳለን። ይህ ትውልድ የሀገሩን የቅርብና የሩቅ ሁኔታዎችን ለመረዳት የአካባቢውንና እናት ሀገሩ የምትገኝበት የአፍሪካን አህጉር ሁኔታ፤ ሰፋ አድርጎም የዓለምን ሁኔታ እድሜው፣ እውቀቱና ችሎታው በፈቀደለት ደረጃ ሁሉ ከማየትና ከማገናዘብ አልፎ ተገቢውን ትምህርት ለመቅሰምና የሀገሩንና የወገኑን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ተስማሚ መፍትሔዎችንም ለማግኘት በእጅጉ ጥሯል።

ያ በአገርና በወገን ፍቅር የነደደ ልቦና የነበረው ለውጥ ፈላጊ ትውልድ በወቅቱ ከፊት ለፊቱ ጎልቶ ይታይ የነበረውን ፍጹማዊ የዘውድ አገዛዝና እንዲሁም በዓለም ደረጃም የቅኝ ግዛት መስፋፋትን መንሰራፋትን አጥብቆ ይቃወም ነበር። ለመላው የሰው ልጆች ፍትህና ርትዕን ይመኝ የነበረው የዚያን ወቅት ለውጥ ፈላጊ ወጣት ትውልድ በሀገሪቱ ውስጥ ትምህርትን፤ ሕክምናን እና ሥራን ለሁሉም ዜጋ ለማዳርስ የዜጎችን ሙብትና ጥቅም በዕኩልነት ለማስከበር ፤ ጭቆናን ለማስወገድ፤ በዕኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነትን ለማሰረፅ፤ ማኅበራዊ ፍትኅን ለማስገኘት ፈጣን ኤኮኖሚያዊና የቴክኖሎጂን እድገት ለማምጣት ትልቅ ዓላማና ብሩህ ተስፋን አንግቦ ነበር የተሰባሰበው፣ የተደራጀውና ለትግል የተሰለፈው። ይህ ክፍል ነው የተጠቀሱትን ክቡር ዓላማዎች በፖለቲካ ድርጅት መልክ ተደራጅቶ ለማራመድ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የሚለውን ሥያሜ ያገኘውን ሕዝባዊ ድርጅት ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በሚያዚያ ወር 1964 ዓ.ም የመሰረተውና ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር የፓለቲካ ፓርቲን መሥርቶ የትግልን ችቦ የለኮሰው። ኢሕአፓ በተመሠረተበት ወቅት ስለአደረጃጀትም ሆነ ስለፖለቲካ ትግል በአርአያነት ሊያገለግለው የሚችልና ተመክሮውንም በማገናዘቢያነት ሊጠቀምበት የሚችል ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲ አልነበረም። በአፄው ሥርዓት በምትመራበት አገር ውስጥ በፖለቲካ መደራጀት አይፈቀድም ነበር። በመሆኑም በህቡዕ የተመሠረተው ኢሕአፓ በአገራችን የፖለቲካ ታሪክ አዲስ ምዕራፍን የከፈተ እና አዲስ ተስፋን የፈነጠቀ ነበር ማለት ይቻላል።

የድርጅቱን ታሪክ መለስ ብለን ስንቃኝ የምንቀስመው ትምህርት ቢኖር፤ በኢሕአፓ ውስጥ የተሰባሰቡት አባላቱና ደጋፊዎቹ ከመላው የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰባሰቡ፤ እድሜና የእውቀት ደረጃቸው በፈቀደላቸው አቅምና ችሎታ የአገራቸውን ታሪክ ለማውቅ የሞከሩ፤ የሚታገሉለትን ሕዝብ ሥነልቦና የተረዱ፤ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ፆታ ሳይገድባቸው ማንነታቸውን ኢትዮጵያዊ አድረገው የተሰባሰቡ ሀገር ወዳዶች ነበሩ ብሎ በአጭሩ መግለፅ ይቻላል። በኢሕአፓ ዙሪያ የተሰባሰቡት አባላቱና ደጋፊዎቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ ከደቡብ ወደ ሰሜን፣ ከምስራቅ ወደምዕራብና ሰሜን እና ደቡብ ወዘተ፣ ወዘተ... በተደረገ መስተጋብር የተሳሰረና የተጋመደ ነው የሚል ጽኑ እምነትን የተጎናጸፉ ነበሩ። የሚኖሩባት አገር የብዝኃነት ታሪክ ባለጸጋ የሆነች ጥንታዊ ሀገር ነች ብለው የሚያምኑ ሲሆን ኢትዮጵያ የተገነባችውም በዲሞክራሲና በውይይት ሳይሆን ኩታ ገጠም በሆኑም ሆነ ተራርቀው በሚገኙ አካባቢዎች በተነሱ አገዛዞች ሠይፍና ጦርነት፣ በፈሰሰ ደምና በተከፈለ የሕይወት

መሰዋዕትነት ጭምር ነው የሚለውን በሚገባ የተረዱና ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንበትን ሥርዓት ለማረጋገጥ የቆሙ፤ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሆነችውን የነፃነት አርማ፣ ሰንደቅ ዓላማ መለያቸው ያደረጉና የኢትዮጵያን ግንባታንና የኢትዮጵያዊነትን ጽንሰ ሀሳብ ማጎልበት ሀገራዊ ኃላፊነታቸው አድርገው የወሰዱ ነበሩ።

ኢትዮጵያዊነትን አንድ ሥርወ መንግሥትም ሆነ ሌላ አካል ልፍጠርህ ብሎ በሥነ-ምርምር (በላቦራቶሪ) የቀመረውና የፈጠረው ሳይሆን ፤ ኢትዮጵያ እንደ አገር እውን ከሆነች ጀምሮ በውስጧ ህልው ሆኖ የኖረው ሕዝብ ባልተቋረጠ መስተጋብር ተጋምዶና ተሳስሮ የወለደው ማንነት ነው። ለዚህም ማስረጃው፣ ባለሀገሩ በክፉ በደጉ፣ በማግባት በመፍታት፣ በመሞት በመውለድ፣ በመጣላት በመፋቀር፣ … ሂደት የኖረባትና በጋራ የኔ የሚላት ምድር፣ በጠላት ስትደፈር የዛገ ብረቱን በመቅን ወልውሎና የሰቀለውን ዝናር ታጥቆ፤ ያለውን ጎራዴ መዞ እምቢኝ ለሀገሬ ኢትዮጵያ እያለ እርፍ መጨበጥ ከጀመረው ልጁ ጋር በየዳፋውና በየሸለቆው ሊታደጋት የክብር መስዋእትነትን ሲከፍል የኖረና አሁንም እየከፈለ የነበረና ያለ መሆኑ ነው። ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው ዜጋ ሁሉ ዛሬም ለዚህ እውነተኛ ምስክር መሆኑን ማንም ሊክደው አይችልም።

ያ ትውልድ ኢትዮጵያዊነት ከአንድ ኩሬ ብቻ የተቀዳ ማንነት ሳይሆን በአማራው ደጃፍ የኦሮሞው፤ በኦሮሞው ደጃፍ የጉራጌው ፤ በሲዳማው ደጃፍ የወላይታው፤ በሱማሌው ደጃፍ የአዳሉ፤ በትግሬው ደጃፍ የአገው፤ በከንባታው ደጃፍ የኩሎው፤ በጉሙዙ ደጃፍ የሽናሻው፤ ወዘተ፣ ወዘተ… አልፎ ሀያጅ ግኙኝነትና መስተጋብር የተፈጠረ ታሪካዊ እሴት መሆኑን የተገነዘበ ትውልድ ነው። ያ ትውልድ ኢትዮጵያዊነት በአንድ ጀንበርና በአንድ አካባቢ ብቻ የተጸነሰ ሳይሆን የብዙ ሺህ ዓመታት የኢትዮጵያ ታሪክ ጉዞ ውጤት ነው ብሎ የሚያምን፣ ከማንምና ከምንም በላይ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ያስቀደመ ትንታግ ትውልድ ነው ተብሎ ሊገለፅ የሚችል ነው። ስለ ሀገር ግንባታ ሲነሳም፤ ከሀገራችን ታሪክና የሀገር ግንበታ ጋር የእኩልነት ጥያቄ የተያያዘ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ባይ ነው። ያ ትውልድ በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ዘመናትን ያስቆጠረ ሰፊ የሆነ ትግልና ከፍ ያለ መስዋዕትነትንም ከፍሎበታል። ዛሬም እየተከፈለበት ይገኛል።

ፍትኀን እኩልነትና ዴሞክራሲን ለሀገሩ ይመኝ የነበረው ተራማጁና ለውጥ ፈላጊው ወጣት ትውልድ፣ የሚወዳት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ፀንታ፤ የሀገር ግንባታ ሂደትዋ ሊቀጥል የሚችልባቸውን ዘዴዎች በማሰብና በመመራመር በጊዜው መፍትኄ ሊሆኑ ይችላሉ ያላቸውን ዜዴዎችና ትልሞች መሠረት ያደረጉ የመፍትኄ ሀሳቦችን ጭምር መሻት የጀመረ ታታሪ፤ ለሀገርም በጎ አሳቢና ለውጥን ፈላጊ ትውልድ ነበር ። ዛሬም ነው።

ያ ትወልድ የሀገር ግንባታና የዜጎች የእኩልነት ጥያቄ የማይነጣጠሉ መሆናቸውንና የሀገሪቷን ታሪክና ኢትዮጵያ የነበረችበትን ተጨባጭ ሁኔታ በመረዳት ከነበርችበት ኋላ ቀር ሥርዓት ተላቃ በልማትና የእድገት ጎዳና የምትጓዝበትን ራዕይ የተለመ ብርቅዬ ኢትዮጵያዊ ትወልድ ነበር ማለት ይቻላል። የዚያ ትውልድ ራዕይ የነበረው ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንደትቀጥልና ለሀገር ግንባታ ደንቃራ የሆነውን የ"ሞትን" ያህል ይፈራ የነበረውን የመሬት ጥያቄን እንዲሁም አብሮ የእኩልነትን ጥያቄ መዞ በማውጣት መፍትኄ እንዲበጅለት ድምፁን በአደባባይ ያሰማ ብቻ ሳይሆን የችግሩንም መፍቻ ቁልፍ የጠቆመ፤ የታገለና ያታገለ፤ ዛሬም በፅናት ለዚሁ እያታገለ ያለ ትውልድ ነው።

የዚያ ትወልድ አካል የሆነው ኢሕአፓ የችግሮች ሁሉ ችግር የሆነውን የመሬት ጥያቄ አበጥሮ በማውጣት የመፍትኄ ሀሳቦችን በድርጀቱ የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ ያሰፈረ የመጀመሪያው የፖለቲካ ድርጀት ሲሆን "መሬት ለአራሹ ለላብ አፍሳሹ!" ሲልም በአደባባይ ድምጹን ከፍ አድርጎ ከአድማስ እስከ አድማስ አስተጋብቷል። ጥያቄውም የመላው የኢትዮጵያ

አርሶ- አደሮች ጥያቄ በመሆኑ በመላ የአገሪቱ ክፍሎች ሕዝባዊ ትግሉ በየአቅጣጫው እንዲቀጣጠል ረድቷል። ኢትዮጵያ ውስጥ ለነበሩ በርካታ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚዊና ማኅበራዊ ችግሮች መፍትኄ ለማግኘት ትውልዱ በፖለቲካ አካል ውስጥ መደራጀትና መታገልን ግዴታው አደረገው። ለችግሮቹ መፍትኄ ሊገኝ የሚችለውም ሕዝብ የሥልጣን ምንጭነቱና የሥልጣን ባለቤትነቱ ሙሉ በሙሉ መረጋገጥ ሲችል ነው በማለትም አቋሙን በግልጽ አስተጋባ። ለስኬታማነቱም ሁሉም የኅበረተሰብ ክፍል ሳያሰልስ በመደራጀትና በመታገል ሙብቱንና ጥቅሙን ማስጠበቅ እንዳለበት አጥብቆ አሳሰበ።

ዛሬም ያ ትወልድ ያነሳቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች አልተመለሱም። በ1966 ዓ.ም የመንግሥት ሥልጣን ከሕዝብ እንዲመነጭና በሕዝብ ቁጥጥር ስር እንዲሆን ኢሕአፓ ያነሳው ጥያቄ ዛሬም ድረስ ህያው ነው። ሕዝባዊ ሥርዓትን ለመመሥረት በአገዛዞችና በሕዝቡ መሀከል የሚደረገው ትግል አሁንም አታካችና አድካሚ ብቻ ሳይሆን እልፍ አዕላፍ የሆነ መስዋዕትነት ከማስከፈሉም ሌላ የሀገርን ልማትና እድገት የጎዳ፤ ኢትዮጵያን ለአደጋና ለብተና ያጋለጠ፤ መቋጫ ያልተገኘለት እልህ አስጭራሽ ትግል ሆኖ ቀጥሏል። ከዛሬ 49 ዓመት በፊት (ሚያዚያ 4 ቀን 1964ዓ.ም) ኢሕአፓ ሲመሠረት ጀምሮ እንደ ድርጅት ይዞት የተነሳው ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ በአግባቡ ምላሽ እስካላገኘ ድረስ ትግሉ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ የሚሄድና የሚቀጥል ይሆናል። አምባገነኖችንም ፋታ መንሳቱና መታገሉ የማይታበል ሐቅ መሆኑን አስቀድሞ የተረዳ ለመሆኑ ደግሞ አሁን ያለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በቂ ማስረጃ ነው። ለዚህም ለሚወዷት አገራቸውና ለሚያከብሩት ሕዝብ ከቡር ህይወታቸውን ሳይሳሱ መስዋዕት ለሆኑ ለነዚያ ለውጥ ናፋቂ ኢትዮጵያዊያን ጀግኖቻችን የማያቋርጥ ክብርና ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል።

በአገራችን የፖለቲካ ታሪክ የአገር መሪዎች እንደ ጣዖት ሲመለኩና ፤ እንደ ታቦት ሲሰገድላቸው ፤ እንደ ጭራቅ ሲፈሩ ስለነበር በአደባባይ ሲቀጥፉና ሲባልጉ ከመደንገጥ በስተቀር ሥራቸውን መተቸት፤ በሀገሩ፥ ሰለሀገሩ ለምን እንዲህ ሆነ? ለምንስ እንዲህ ይሆናል? ብሎ መጠየቅም ሆነ መጻፍ ወይም መናገር እንደ ወንጀለኛ የሚያስቆጥር፤ መቀመቅ የሚያስወርድ ብቻ ሳይሆን ከቡር ህይወትን የሚያስገብር መሆኑ የትናንት ትዝታ ሆኖ መቅረት አልቻለም። ይባስ ብሎ ዛሬም ይኸው ድቅድቅ ጨለማ ሰፍኖ በተፋጠነ ሂደት ፍጥነቱን ጨምሮ ሀገራችንን የዋይታ፥ የሰቆቃና የእልቂት ቤት እንድትሆን አደርጓታል።

ዛሬ በሀገራችን ላይ ያንዣበበውን የፖለቲካ ድባብ በጥልቀት ስንመረምር ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለመበታተን በየራሳቸው እኩይ የቤት ሥራ የተጠመዱ ዘረኞች የሚርመሰመሱባት ሀገር መሆኗን ማየት ይቻላል። በሀገራችን ሰፍኖ ለሚገኘው የርስበርስ ግጭት፥ ደም መፋሰስ፥ መፈናቀልና አጽያፊ የፖለቲካ መልክዓ-ምድር ክስተት ሀገሪቷን የዳረጋት ከአባቱ ከወያኔ የወረሰውን ሕገ-አራዊት የሆነውን የዘረኞች ሕገ-መንግሥትን አስቀጥላለሁ ባዩ የአገዛዙ ሹም ነው። በዚህም የተነሳ አገር እየታመሰችና የዘር ማጥፋት ወንጀል እየተፈፀመ ነው። ሹሙ እንደወረደ ከአባቱ ከወያኔ የወረሰውን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይመክርበትና ይሁንታውን ሳይሰጠው የተጫነበትን፣ በእጅጉ ያስመረረውንና እንዲወገድለት የሚፈልገውን የአራዊቶች ሕገ-መንግሥት እንድንቀበልለት፣ እንድንወድለት፤ እንድናወድስለትና እንድንገዛበት ይመኛል። ከሹሙ የሚወደድ ተግባርም ሆነ አሜን ብሎ ለመቀበል የሚያስችል ፖለቲካዊ፥ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፖሊሲ አላየንበትም። ሹሙ ያለው ችሎታ የሕዝቡን ጥያቄ እየነጠቀ በጣፈጡ ቃላት ህልውናዋን ጠብቃ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈችውን የሀገራችን ኢትዮጵያን ስም እያንቆለጳጰሰ ማላዘኑ ሲሆን በተግባር ግን ሀገራችንን እያፈረሰብን ነው። በዛሬው ጊዜ ፖለቲካ ማለት የሰውን ልብና አዕምሮ ማሸነፍ ሆኖ ሳለ በጉልበት መተማመንም ሆነ፤ በአፈጮሌነት ተሙለጭልጮ ለማለፍ መሞከር እራስን ያጋልጣል፣

ያዋርዳልም። ሹሙ ሕዝብ የሚያውቀውን የተራራ ግዝፍት ያህል ያለውን ሐቅ አምታትቶና ሸውዶ ለማለፍ የሚያደርጋቸው ሙከራዎች ወደ ገደል የሚውስድ የቁልቁለት ጉዞ ውስጥ አስገብተውታል። **“ለዚህ ስንዴ እየለመነና እየሰፈረ ለሚኖር ሕዝብ ዴሞክራሲ ምኑ ነው”፤ እኛ ዘንድ ሰርፐራይዝ (ድንገተኛነት) የለም፤ እናውቀዋልን፤ አሁን የሚደረገውን ጨኸት እናውቀዋለን፤ ብዙ ልምድ ስላለን ቅንጣት ታክል ጫና የሚፈጥርብን አይደለም”** በማለት ያሰማቸው ድንፋታዎች ሹሙ ለሕዝብ ያለውን ንቀት በማሳየት በኩል ለናሙና የሚቀርቡ የፖለቲካ ክስረቶቹ ናቸው። ሹሙ ሕዝብን ንቋል። እራሱንም በአደባባይ አጋልጧል። ሊነግሥብን እየተንደረደረብን ለመሆኑ ከዚህ በላይ ማስረጃ ማቅረብ አይጠበቅብንም። ባለፉት ሶስት ዓመታት ኢትዮጵያን ያሉና ለሀገራቸው ሉዓላዊነት የቆሙ፤ ለዚህች አገር ሕዝብ ፍትኅና ዴሞክራሲን የተመኙ ዜጎች ዛሬም ሲጋዙ፥ ሲገደሉና ሰቆቃን ሲቀበሉ እያየን ነው። በዚህም ተባለ በዚያ አሁንም የሹሙ ጥረት አደናግሮም ሆነ ፍጅትን አካሂዶ ከየአቅጣጫው የገነፈለውን የሕዝብ ብሶት/ አመፅ ማፍንና ማስቆም ነው። ለዚህም ሠይጣናዊ ተልኮው የሚተበብሩትን አድርባዮችና እበላ ባዮችን በየአቅጣጫው አሰማርቷል። ሹሙ ተሻጋሪውም፣ አሸጋጋሪውም፥ ገዥውም እሱ ራሱ መሆኑን አስረግጧል። ሹሙ ከስረመሠረቱ ዘረኛ ብቻ ሳይሆን ጸረ-ኢትዮጵያም ጭምር መሆኑን አላምን አልቀበል ብለው ወይም ግራ ተጋብተው ልብና ጆሮ የሰጡትን ሁሉ ያስቆጣና ያስመረረ ወደ ተቃውሞው ጎራ የሰደደ መሆኑ በገሀድ የታየና እየታየም ያለ ሐቅ ነው። ለሹሙ ዴሞክራሲ ማለት ቧልት ማወናበድና ማስመሰል መሆኑን በአንደበቱ ብቻ ሳይሆን በተግባር አረጋግጧል። ትናንት በዘመነ ወያኔ ያየነው ዛሬ በዘመነ ሹሙ እየተደገመብን ነው። በዘመነ ወያኔ ምርጫም ከዴሞክራሲ የተጣላ፤ ወያኔ ራሱን በራሱ መርጦ የሚሰይምበት ሂደት መሆኑን ለ27 ድፍን ዓመታት ታዝበናል፤ ዛሬም እየቀጠለ ያለውና የሚታየው ቲያትር ከዚህ የባሰ እንጂ የተሻለ እንደማይሆን መጽሐፍ ገላጭ መሆን አያስፈልገንም።

አዕምሮ እያላቸው ማሰብ፤ ዐይን እያላቸው ማየት ፤ ጆሮ እያላቸው መስማት አቅቷቸው ለአደጋ የሚጋለጡ ሁሉ ሊወቅሱ የሚችሉት ራሳቸውን ብቻ ነው። ከስህተት ታርሞና ራስን ወቅሶ፤ አገርንና ሕዝብን ለማዳን ከሚደረገው ትግል ጎራ ተሰልፎ ለሀገር መቆሚያ ጊዜው አሁንም አልመሸምና የሚሰማ ጆሮ ያለው አገርን ከሚያፍርሱ ጎጠኞችና አስመሳዮች ራስን ማራቅ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ግዴታ ጭምር መሆኑን እያስገነዘብን ለጋራ ትግል ጥሪያችንን እናስተላለፋለን።

መንግሥት አንዱ ባንዱ ስለተለወጠ ወይንም ስለተፈነቀለ፤ አንዱ ወርዶ ሌላው ስለወጣ፣ ተኪው ወይንም ፈንቃዩ ስለ ሕዝብ አንድነት፤ ስለ ኢትዮጵያ ታላቅነት፤ ስለ ሰላምና ዴሞክራሲ ለወጥ ባለ አንደበትና የሕዝብን ስሜት በሚኮረኩር መንገድ ስለ ሰበከ የሀገር ህልውና ዋስትና ሊያገኝ አይችልም። ሀገር ሀገር የምትሆነው የውስብስብ ችግሮቿ መፍትኄ በቀጥታ ከብዙኀኑ ሕዝብ የሚመነጭበት፣ ሂደቱም በአንድ በተወሰነለት ቦይ ብቻ የሚፈስ ሳይሆን በብዙ አፍላጋት በዚህም በዚያም ገደብ ሳይደረግበት እንዳሻው የሚወርድበት ሰፊ ዴሞክራሲያዊ መንጣለያ የሚሰጥ ሕዝባዊ የሆነ ሥርዓት/መደላድል ሲገነባ ብቻ ነው። ለዚህም ምስክሩ አገራችን ያሳለፈቻቸው ሕዝባዊ ማዕበሎችና የተፈራረቁባት አምባገነኖች በሕዝብ ላይ የፈፀሙት ሕዝብ ይቅር የማይለው በደል በቂ ምስክር ነው። ትናንት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አወድሱኝ የሚል ምልክት ሳያሳይ ከቶውንም ሳያስበው ሁሉም እየተሽቀዳደመ አወዳሽና አድናቂ ሆነ፤ እሱም ሁሉን አዋቂ የበቃሁና የነቃሁ መሪ ነኝ ሲል ተኮፈሰ! ቆራጥ ነው ተባለ ፤ “ከታላቁ መሪ ጋሪ ወደፊት!” ተብሎ ሲጨበጭብለትና ሲሰገድለት መቁረጥና መፍለጡን በፀሐይ ብርሃን ፍጥነት አጣደፈው። ኮሎኔሉ አንድ ትውልድ መትሮ ፤ ሀገሪቷን ለጽንፈኞች አስረክቦ በመጨረሻም አገር ጥሎ ፈረጠጠ። የኢትዮጵያ ሕዝብ መከራና ፍዳ ግን ቀጠለ።

በአገራችን ታሪክ የአገርን ሉዓላዊነት ያስደፈረውንና ተዋልዶ ተዛምዶና፣ ተዋዶ ለዘመናት በአንድ ሀገር ይኖር የነበረውን ሕዝብ፣ በጎጥ ከልሎና ከፋፍሎ የአፓርታይድ ሥርዓትን በአገራችን ምድር ዕውን ያደርገን የጎጠኞች መሪ፤ የአገሪቱ ብርቅዬ ምሁራን የፈለቁበትን የአዲስ አበባን ዩነቨርስቲ ምሁራንን አባሮ ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊስን ለተገበረው መለስ ዜናዊ "የመለስ አካዳሚ" ገነባንለት ሲሉ በሕዝብና በሀገር ላይ አፌዙበት። "እንደ መለስ ዓይነት መሪ በመቶ ዓመት አንዴ ቢፈጠር ነው" ሲሉም በሕዝብ ላይ ተሳለቁበት። መለሰም ሆነ ድርጅቱ ወያኔ ጊዜ ጥሏቸው ተንኮታኮቱ። የተከሉት የዘር መርዝ ግን ሀገሪቷን ማመስ ቀጥሏል።

ዛሬም ከዚህ ዓይነቱ አባዜ አልተላቀቅንም። "አገር መሪ አገኘች!" ተባለ ፤ "ከእግዚአብሔር የተላከ ሙሴ" ተብሎ ጫማው ተሳመለት። ስለኢትዮጵያ ትንሣኤም ተዘመረ፤ አዲሱን ሹም መቃወም በአሪዎስነት የሚያስፈርጅም ሆነ። ብዙም ሳይዘልቅ የሹሙ ምንነትና ማንነት ጭምብሉ ሲገለጥ በአደባባይ ተጋለጠ። ከተዋናዮቹ መቀየር ሌላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም ተመሳሳይ ተውኔት ለማየት ተገደደ። "ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም" እንዲሉ ሹሙ መላ ካቢኔውን ሰብስቦ የውሃ መሀንዲሱ እሱ፤ የግብርና ኤክስቴንሽን ኤክስፐርቱ እሱ፤ የትምህርት ሚንስትሩ እሱ፤ የእስታስቲክስ ፕላን መምሪያው እሱ፤ የጤና ሚንስትሩ ራሱ፤ ... ወዘተ ፤ ሁሉን አዋቂ እሱ ሆኖ የቀድሞውን ኮሎኔል አስናቀ።

ዛሬም ይህ የሕዝብን ልዕልና መሻሩና በእኔ አውቅልሃለሁ የመሰየም መርገምት የቀጠለ ለመሆኑ ከላይ በጥቂቱ ያሰፈርናቸው የገዥዎች/የአምባገነኖች የጋራ አስነዋሪ ባህሪዎች በቂ ማሳረጃዎች ናቸው። አምባገነኖች መሠረታዊ ይዘታቸውና እምነታቸው የሕዝብን የበላይነት የሚቃወም በመሆኑ የሕዝብን ልዕልና (የሕዝብን የባለሙሉ ሥልጣን ባለቤትነት) መቀበል መጥፊያችን ነው ብለው ስለሚያምኑ የሥልጣን ጥማታቸውን ለማርካት የሚያዳምጡት ራሳቸውንና ወጥሮ የያዛቸውን ትምክህት ብቻ ነው። ዛሬም በገሀድ የሚታየው ይህ ሕዝብን የመናቅ አባዜ በሁሉም አቅጣጫ ተከስቶ እንደቀጠለ ነው።

በሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላም የሰማይን ያህል ርቋል። ሕዝብ በሰላም ወጥቶ በሰላም መግባቱን፤ በሰላም አድሮ መንጋቱን በጉጉት የሚናፍቅባት አገር ሆናለች። ስለአንድነትና ስለኢትዮጵያዊነት ከቦታ ወደ ቦታ ተዘዋውሮ መስበከና በኢትዮጵያዊነት መደራጀት የህይወት ዋጋን ያስከፈላል። ትናንት በዘመነ ወያኔ በማንነት የተጀመረው መፈናቀል፥ መሰደድና ግድያ በተረኛ የኦሮሞ ጽንፍኞች ተጠናክሮ ተስፋፍቶ ቀጥሏል። በአማሮ፥ በጌዲኦ፥ በጉጂ፥ በወለጋ፥ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፥ በጂማ፥ በመተከል፥ በሁሮ ጉድሮ፥ በሰቆጣ፥በአከሱም በማይካድራ፥ በጉራፈርዳ፥ በሸዋሮቢት፥ በአጣዬ፥ በማጀቴ፥ በካራቆሬ፣ ...ወዘተ በአማራው ላይ የሚደረገው የዘር ማጥፋት ወንጀል በተደራጀና በተቀነባበረ መንገድ በአገዛዙ መዋቅር ሽፋን ተጠናክሮ በሰፊው ቀጥሏል። ዛሬ በመላው የአገሪቱ ክፍሎች የንጹሐን ደም እንደ ጅረት ውሀ ይፈሳል፤ የህጻናት አስከሬን በየጢሻው ተጥሎ የአሞራና የዱሩ አራዊት ሲሳይ ሆኗል። ለዚህ ሁሉ መረን የለቀቀ ግፍና በደል በዋናነት ማነው ተጠያቀው ቢባል መልሱ የጎጥ ፖለቲካው ሥርዓት አራማጆችና የአገዛዝ ቁንጮ የሆነው አዲሱ ሹም ኮሎኔሉ ናቸው የሚል ነው።

ሹሙ በዙሪያው የኮለኮላቸው ባልሥልጣናትና አማካሪዎች አብዛኛው በዘር ሀረግና በእምነታቸው ሳይቀር ተመርጠው የተሾሙ፤ አድርባይና የጎጠኛው ሥርዓት አራማጆች ናቸው። በዙሪያው መኮልኮላቸው ብቻ ሳይሆን ያላቸውን የመንግሥት መዋቀር ተገን በማድረግ ለአሸባሪው ኦነግ ሠራዊት አስፈላጊውን እገዛ ፤ ከለላና መከታን የሚያደርጉ ለመሆናቸው በየቀኑ የሚፈሰው የንጹሀን ደም ምስክር ነው። በመሆኑም ይህንን አገዛዝ የአጀቡትም ሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚደግፉና የሚረዱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚፈጸመው ሰቆቃ ግፍና በደል በታሪክ ፊት ተጠያቂና ተወቃሽ ከመሆን አይድኑም።

ሀገር ስትፈርስና ስትታመስ ፤ ሀጻናት በገፍ ሲታረዱ ፤ ሕዝብ ከቄዬው ሲፈናቅልና ንብረቱ ሲጋይ ሚሊዮኖች ሲራቡና ሲታሪዙ "ትዕግሥት ያሻል" እያለ የሚያሾፍ ዘመናዊ ሹም መዳፍ በሥልጣን ተኮፍሶ ይገኛል። መንግሥት የሚባለው ተቋም የመላው ሀገሪቱን ሕዝብ ከ እስከ ከ ሳይለይ የዜጎችን መብትና ነፃነት፤ በእኩልነት ጠብቆ ትክክለኛና ፍትሃዊ የሆነ ሥርዓትን ማክበርና የማስከበር ብቃትና ችሎታ ሊኖረው ይገባል። "የአንድ አገር ዜጎች በማንነታቻው ልዩነት ሳይደረግ በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ እኩል የሆነ የሕግ ጥበቃም ይደረግላቸዋል" የሚለው ድንጋጌ የዓለም መንግሥታት ሁሉ የተቀበሉትና ያፀደቁት ውሳኔ ሲሆን ይህን በኩረ ሀሳብ ለይስሙላ ሕገ-መንግሥት ተብየው ውስጥ ማስገባት ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ መተግበር የመንግሥት ኃላፊነትና ግዴታውም ነበር። መንግሥት ዜጎቹን ከማንኛውም ዓይነት አድሎ፥ ጥቃት፥ በደልና ተፅእኖ ሊጠብቃቸውና ሊከላከላቸው ይገባል፤ ኃላፊነትም አለበት። ኢትዮጵያ የኢትዮጵያዊያን ሁሉ በመሆንዋ በውስጧ የሚኖሩ ዜጎቿ ያለስጋት እንደልባቸው በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ተንቀሳቅሰው የመሥራት፣ ንብረትን የማፍራት፣ ቤተሰብ የመመሥረት ባጠቃላይም የመኖር መብታቸው ሊከበር ደህንነታቸውም ዋስትና ሊያገኝ ይገባል።

ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ፤ የሙያና የሲቪል ማኅበራትን መሥርተው ለመንቀሳቀስ የማንም ሞግዚትነት አያሻቸውም። መንግሥት የተቋማቱን የውስጥ ነፃነት መዳፈር ወይም በጉያው ተወሽቀው አጫፋሪና አጨብጫቢ እንዲሆኑ ፍላጎትና ምኞት ቢኖረው እንኳን ሕግ ሊያግደውና ሊጠይቀው ይገባል። የአንድ መንግሥት ትክክለኛ ተግባር የሀገሪቱንና የዜጎቹን አንድነትና ሉዓላዊነት ማስከበር በሕዝቡ መካከል የመቀራረብና በፍቅር አብሮ የመኖር ስሜት፤ የአንድነት (ሀገራዊ) ስሜት መፍጠር፤ ሕግና ሕጋዊነትን ማስከበርና ማክበር፤ የሕዝብን ችግርና ብሶት አድምጦ ተገቢውን ዳኝነት መስጠት፤ሀገሪቱንና ዜጎቿን በውስጥም ሆነ በውጭ የተሰሚነታቸውን ክብርና ልዕልና ከፍ ማድረግ፤ ዘረኝነትን፣ ጠባብና ክልላዊ ስሜትን፣ ጥላቻን የሚሰብኩና ሕዝብን የሚያጫርሱ ቡድኖችና ግለሰቦችን ሕጋዊነት መንፈግ ብሎም ለሕግ ማቅረብ የመንግሥት ኃላፊነት ነው። በአጠቃላይ በሕዝብ መካካል በቀልና ቂም ከሚያነሳሱና ከሚቀሰቅሱ መሰሪና ነውረኛ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ባህል ከማስፋፋት እንዲታቀቡ ማድረግ የመንግሥት ተቀዳሚና ዋነኛ ተግባሩ ነው።

ከላይ በአጭሩ የተገለፁት የመንግሥት መሠረታዊ የሆኑ ተግባራትን በተጫባጭ ስንመረምር አገሪቷና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ፣ አሁን በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ነው ያሉት የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ እንድናነሳ የግድ ይላል። በአገራችን ዛሬም እንደትናትናው የተለወጠ ነገር የለም። የተለወጠው ወያኔ/ኢሕአዴግ የሚለው ጭምብል ኦህዴድ/ብልጽግና በሚለው መተካቱ ብቻ ነው። ዛሬም እንደትናንቱ የመንግሥት ሥልጣን ሙሉ በሙሉ ተጠቃሎ በአንድ ቡደን (በአንድ ግለሰብ /በአዲሱ ሹም) እጅ በገባበት፤ ነጋ ጠባ የብልጽግና ነጋሪት ቢመታ እምቢልታ ቢነፋ ዛሬም አገራችን የዋይታ ቤት ከመሆን አልዳነችም። ሕዝቡ ከድህነት አረንቋ አልተላቀቀም። በአንድ አገር ውስጥ ለሚኖር ሕዝብ እኩልነት፥ ፍትህ፥ ደህንነት፥ ዴሞክራሲ፣ የሰብዓዊ መብቶች፣ ...ወዘተ በተሟላ መንገድ መረጋገጣቸው ለብልጽግና ለዕድገት አስፈላጊ መሠረቶች ናቸው። ዳቦና ሥራ፥ የሌለው፣ ጤንነቱ የተጓደለ፣ የደህንነት ዋስትናው ያልተረጋገጠለት ሕዝብ ኢትዮጵያን አበልጽጋት መባሉ "በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት" ከመሆኑም በላይ በሕዝብ ላይ ከማፌዝ ያለፈ ወንጀል ጭምር ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በኦሮሞ ፅንፈኞች የዘር ወረርሽኝ ተጋልጣ ህልውናዋ በየቀኑ እየተሸረሸረ መሆኑ ግልጽ ነው። በሹሙ የሚመራው የኦሮሞ ብልጽግና ተብዬው የጎጠኞች ስብስብ ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያዊነት አላቅቆና ገነጣጥሎ፤ ሰባብሮና አሽመድምዶ ሊያጣፋት የተሰየመ መሆኑን ጠንቅቆ ማውቀና መገንዘብ ተገቢ ነው። ሹሙ ለሥልጣን የበቃው ሀገር ወዳዱ

ዜጋ ለወያኔ በነበረው ጥላቻ ተዘናግቶ በውዥንብር ተወናብዶና ተጠምዶ ሹሙን ከወያኔ ኮሶ ያሸረናል በሚል ተስፋ ጭፍን ድጋፉን በመስጠቱ እንደነበር የሚረሳ አይደለም።

ራሱን ያወቀ ጠላቱን ያውቃል የሚለውን ብሂል ዘንግተን፤ ተጨባጩን እውነታ መመልከት፥ መመርመርና መገንዘብ ተስኖን፣ ራሳችንን ለቀቢፀ ተስፋ አስገዝተን ሕዝቡንም አዘናግተን አገር አልባነታችንን እያረጋገጥን ነው። አገር በአገር አፍራሾች አባዜ እየተናጠች ነው። ኢትዮጵያ እንድትፈርስ እያናጣት ያለው ዘረኝነት ነው። የአገራችንን ሉዓላዊነት እያስደፈረ፤ አገርን በሁለንተናዊ መስክ እያዳከመ ለጽንፈኞች ሽፋን ሰጥቶ አማራውንና ኢትዮጵያን እያስጠቃ ያለው የአገዛዙ ሹም ነው። ሹሙ ሥልጣኑን በብቸኝነት የተቆጣጠረው፥ የጠቀለለውና እዚህ ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለው ብቻውን ባደረገው ጥረት ሳይሆን፤ የሱን ዓይነት ላባ ባላቸው እንዲሁም በእበላ ባዮች አድርባይ ምሁራን ድጋፍ ትብብርና እርዳታ ጭምር ነው። ጠማማው ከየአቅጣጫው ተቆርጦ የፋስ ማስገቢያ ሆኗል። ነጋዴ ፖለቲከኞች በሙብዛታቸው የተነሳ የትግል ይዘት ማንና ምንነት ቅጥ አምባሩ እየጠፋ መጥቷል። የተቀነባበረ ውሸትም ተደጋግሞ ሲቀርብ እውነት ሊመስል ይችላል። ሹሙ ይዋሻል ብቻ ሳይሆን ደጋግሞ ይቀጥፋል። ወያኔም በፈጠራ ወሬና ውሸት ተወዳዳሪ አልነበረውም - ነገሩ “እሳት ካየው ምን ለየው” እንዲሉ። ሁለቱም ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ነጠኞች መሆናቸውን ጨርሶም መዘንጋት አይኖርብንም። ሐቁን እውነታውንና ተጨባጭ ሁኔታውን በጥሞና ማወቅ የወገንን ድክመትና ጥንካሬን ማወቅ፤ በአጉል ምኞትና በተስፋ አለመነዳት ያሻል። ኢትዮጵያን እንደ ኮሶ ትል ከተጣባ የጎሳ ወረርሽኝ ለማሻር ገና ብዙ መራራ ትግልን ይጠይቃል። ሹሙ የሚወደውን ሥልጣን ሽምቀቆውን እያጠበቀ ሲሄድ መለያው በሆነው ዘረኝነት አማካይነት በኢትዮጵያዊነት የሚኮሩትንና የሚያምኑትን ዜጎች እያባረረ፣ እያፈናቀለ፥ እያስፈጀ፣ ለውርደትና ለችግር እየዳረገ፤ እና ኢትዮጵያን እያዋረደ መቀጠሉ የሚጠበቅ ነው። የዛሬው ሹም እንደፈጣሪዎቹ የወያኔ አመራሮች ሁሉ የሕዝብን ብሶትና ተቃውሞን እንኳን እንደማያስተናግድ በገሀድ አረጋግጧል። የሹሙ መልዕክት እንደመካሪና አሳዳጊው ነጠኛው መለስ እብሪትን መሠረት ያደረገና በኃይል ሞክሩኝ የሚል ነው። አዲስ ነገር የለም። የታየው የኖርነው ያስለቀሰን ያመሰቃቀለን ተባብሶ ተፋፍሞ ቀጥሏል። ወያኔ/ኢሕአዴግ ተባለ አዴፓ/ብልጽግና ሁለቱም አንድ ናቸው - የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ስመ ብዙ ዘረኞች ናቸው። ባለአንድ እራስ መርዛማ እባብ የአገር ጠንቅ፣ አገር አፍራሽነታቸውን ጠንቅቆ በመረዳት ሁሉም በትሩን ያንሳ። በሚቻለው ሁሉ ይሰንዝር። የሹሙንና የአጃቢዎቹን እቅድ ያክሽፍ፤ በሁሉም መስክ ዘረኞችን እንታገል። ለማይቀረው የሕዝብ ድል ተደራጅተን አገራችንና ወገናችንን እንታደግ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

እናቸንፋለን!!!